# የባህል እና ስፖርት ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ታህሳስ 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የስልጠኛ ሞጁል)


<u>አዘጋጆች፡</u>

ዶ/ር ተሾመ በላይነህ

ዶ/ር ሳምሶን ወንድይራድ

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

# ማውጫ


አጠቃላይ መግቢያ ..... i

ምእራፍ አንድ፦ የሙስና ወንጀል ምንነት ..... 1

1.1 የሙስና ወንጀል ምንነት ..... 2

1.2. የሙስና ዓይነቶች ..... 3

1.3. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ..... 5

1.4. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ..... 9

ምዕራፍ ሁለት፡-የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ያለው ተጋላጭነት ..... 18

2.1 የዘርፉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት አጠቃላይ መረጃ ..... 19

2.2. የዘርፉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት መንስኤዎች ..... 21

2.2.1 የተቋማት አደረጃጀት ክፍተት ..... 21

2.2.2 የተጠያቂነት አለመስፈን ..... 21

2.2.3. የተቋም ግልፅነት አለመኖር ..... 23

2.2.4 አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን አለመተግበር ..... 25

2.2.5 የንብረት አስተዳደር ጉድለት ..... 29

2.2.6 የግዥ ስርአትን አለመከተል ..... 30

2.2.7. የሰው ሀብት አስተዳደር ክፍተት ..... 30

2.2.8. የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ተግባርን በአግባቡ አለመከናወን ..... 31

2.2.9. የኦዲት እና ቁጥጥር ሪፖረት አለማስተካከል ..... 31

2.2.10 የግንባታ የፕሮጀክቶች አስተዳደር ጉድለት ..... 32

2.2.11. የታዳጊ ስፖርት ፕሮጄክቶች ምልመላና አስተዳደራዊ ችግሮች ..... 34

ምዕራፍ ሶስት፡- በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉት ጉዳትና የመከላከያ ስልቶች ..... 38

3.1. በባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ..... 39

3.1.1. በተቋሙ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳቶች ..... 40

3.1.2 በሀገር ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች ..... 41

3.2 በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶች ..... 41

3.2.1 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት ..... 42


3.2.2 ወቅታዊ የተጋላጭነት ጥናት ዳሰሳ ማድረግ ..... 42

3.2.3 ግልጽነትን ማስፈን ..... 44

3.2.4. ተጠያቂነትን ማስፈን ..... 44

3.2.5 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ....45
3.2.6 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ....45
3.2.7 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል....45
3.2.8. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና የዋና ስራ አካል ማድረግ....46
3.2.9 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር....46
3.2.10 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት....47
3.2.11 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል....47
የመረጃ / ማጣቀሻ/ ምንጮች....49
አባሪ አንድ : የቅድመ ስልጠና ዳሳሳ መጠይቅ....52
አባሪ ሁለት፡ የራስ መገምገሚያ ቼክሊስት....54
አባሪ ሶስት፡ ለሰልጣኞች የተዘጋጀ ተጋላጭነት ልየታ መለማመጃ....56

## አጠቃላይ መግቢያ



የዓለም ሀገራት ከሚጋሯቸው ዓለም አቀፋዊ ወንጀሎች አንዱ መዋቅራዊ፣ድብቅ እና ረቂቅ የአፈፃፀም ባህሪ ያለው የሙስና ወንጀል ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች፣ብልሹ አሰራሮችና የሙስና ወንጀሎች ልማትን በማዳከም የሀገር ኢኮኖሚ እንዲገታ፤ የሞራል እና የሥነ-ምግባር ቀውስ እንዲባባስ፤ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር፤እንዲሁም ህዝብ በመንግስት እና በህግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርጉ አለም-አቀፋዊ እና ብሔራዊ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የችግሩ ዋነኛ ተጠቂዎች እንደ አፍሪካ ባሉ አህጉራት ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ሀገራት ሲሆኑ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያም በከፍተኛ ደረጃ የብልሹ አሰራሮች እና ሙስና ወንጀሎች ተጠቂ እንደሆነች ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ኢትዮጵያ <<በትራንስፓራንሲ ኢንተርናሽናል>> የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ አሰጣጥ በፐርሰንት 38% ነጥብ፤ ከዓለም ደግሞ ከ180 ሀገሮች 94ኛ ደረጃ እንዲሁም ከአፍሪካ በ15ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች (ትራንስፓራንሲ ኢንተርናሽናል ፣ 2023)፡፡ ይህ ደግሞ በሀገራችን የሙስና ወንጀል ምን ያህል እንደተስፋፋ ማሳያ ነው፡፡

የሥነ-ምግባር ጉድለቶች እና ብልሹ አሰራሮች ለሙስና የሚያጋልጡ እና የሙስና ወንጀል እንዲስፋፋ መነሻ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የሙስና ተግባር ደግሞ ከዝቅተኛው ደረጃ ለምሳሌ አነስተኛ ገንዘብ ከፍሎ ያለአግባብ ጉዳይ እንዲፈጽምለት ከማድረግ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የታክስ፣ የኮንትሮባንድ፣ የግዢ እና የግንባታ ማጭበርበር ደረጃ ከዚያም ባለፈ ቡድኖች ተደራጅተው የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሳኩበት እስከ ሶስተኛው ደራጃ የፖለቲካዊ ሙስና ድረስ የሚደረስ ሊሆን ይችላል (FEACC, 2021) ፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር መስከረም/2014 የተደረገውን አዲስ የመንግስት ምስረታ ተከትሎ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የባህል፣ ኪነ-ጥበብ፣ ስነ-ጥበብ እና ፈጠራ እንዲሁም የስፖርት ዘርፍ ልማትን የተመለከቱ ስልጣንና ተግባራት ተሰጥተውት እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ የሴክተሩ ዓላማዎች፡የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብዝኃ-ባህላዊ ሀብቶችን በማጥናት፣

በመጠበቅ፣ በማልማት፣ እና የማህበረሰብ ስፖርት በማስፋፋት ህብረተሰቡን በስፖርት እንቅስቀሴ በማሳተፍ ተወዳዳሪ የሰው ሃይል በመፍጠርና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ከዘርፉ የሚገኘውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ማሳደግ የሚሉት ናቸው፡፡

ከስልጠናው በኋላ የሚጠበቀው ውጤት በሁሉም የሚኒስቴር መሰሪያ ቤቱ ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩት ሰራተኞች ከሥ-ነምግባር ጉድለቶች፣ ከብልሹ አሰራሮችና ከሙስና ተግባራት የጸዱ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ማስቻል ነው፡፡ ስለዚህ የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሰራተኞች ከዚህ ስልጠና የሚያገኙትን ክህሎት ሲተገብሩ፤ ተቋሙን ከብልሹ አሰራሮች የጸዳ እና ሙስና የሌለበት እንዲሆን በማድረግ ሀገራዊ ተልእኮዉን በአግባቡ መወጣት እንዲችል እና ለሌሎች ዘርፎች እርዓያ እንዲሆን ያደርታል ተብሎ ይታመናል፡፡ የዚህ ስልጠና ትልቁ ግብ ደግሞ ሰልጣኞቹ ከራሳቸውም የስራ ዘርፍ አልፈው ከብልሹ አሰራርና የሙስና ተግባር የጸዳች ኢትዮጵያን በመፍጠር ረገድ የሀገራዊ ንቅናቄ አካል በመሆን የበኩላቸውን እስተዋፅኦ እንዲወጡ ማስቻል ነው፡፡

- **የስልጠናው አስፈላጊነት**

ሙስናን ለመግታት የሙስና ወንጀልን ምንነት፣ አይነቶች፤ ባህሪያት፣ አስከፊነትና የሚያስከትለውን ሀገራዊ ውድቀት ማወቅ ብቻውን በቂ እንደማይሆን ተሞክሮዎች እና በዘርፉ የተሰሩ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በሥነ-ምግባር የታነጸ ሰራተኛ እና ለብልሹ አሰራር የማያጋልጥ የአሰራር መንገድ ማበጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህንንም አልፎ ሊከሰት የሚችል ሙስናን ለመከላከል እና ከተከሰተም ለማጋለጥ የሚረዳ ስልት በየዘርፉ ተለይቶ በተግባር ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ በአንዳንድ ዘርፎች የሚታዩት የሙስና ወንጀሎች ድብቅ እና ረጅም ሰንሰለት ያላቸው፤ እንዲሁም በረቀቀ መንገድ የሚከናወኑ በመሆናቸው ሊደረስባቸው የሚችለው ከፍተኛ ጉዳት ካዳረሱ በኋላ ይሆናል፡፡ ይህ እንዳይሆን በሁሉም ዘርፍ ስር ያሉ ሰራተኞች ንድፈ-ሀሳባዊ እዉቀት ብቻ ሳይሆን ከሥነ-ምግባር ጉድለት እና ብልሹ አሰራር እንዲሁም የሙስና ወንጀል ተዋናዮች በላይ ልቀዉ በመገኘት ሙስናን ለመከላከል እና ለመግታት ተግባሪዊ ክህሎቶች ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በየዘርፉ ልዩ ባህሪ ያላቸውን ብልሹ አሰራሮችን እና የሙስና ወንጅሎችን በመለየት ከዘርፉ የሙስና ባህሪ ጋር የሚመጣጠን ህጋዊ እና እስትራቴጅካዊ ስልቶችን ለመተግበር እንዲቻል የሰራተኞች የዘርፍ ትኩር ስልጠና አስፈላጊ ነው፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በስሩ ብሔራዊ ቤተ-መዛግብት እና ቤተ-መጻሕፍት አገልገሎት ፤ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፤ የብሔራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር ዘርፎች ይገኛሉ። ዘርፉ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣጥ የስነምግባር ጉድለቶች፣ ብልሹ አሰራሮች እና የሙስና ተግባራት ምን ያህል እንቅፋት እንደሆኑበት በጥልቅ ጥናት የመለየት ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህም አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር በሙስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶች ላይ የሰራጠኞች የዘርፍ ተኮር ስልጠና አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቷል።



- ### የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

የስልጠናው ዋና ዓላማ ከስልጠናው በኋላ የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሰራተኞች ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን እንዲከላከሉ ማስቻል ሲሆን፤ በተለይ በዘርፉ የሚስተዋሉ የሥነ-ምግባር ጉድለቶችንና ብልሹ አሰራሮችን እንዲሁም የሙስና ወንጀሎችን በመለየት  የመከላከያ ስልቶችን ለመተግበር እዉቀት እንዲጨብጡ፤ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ እና ተጨባጭ ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።

- ### የሞጁሉን ይዘቶች ለማቅረብ የተመደበው ሰዓት

አጠቃላይ በዚህ ሞጁል የቀረቡትን ይዘቶች ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 12 ሰዓት ነው። በመሆኑም አጠቃላይ መግቢያዉን ለማቅረብ 1:00 ሰዓት፤ምዕራፍ አንድን ለማቅረብ 2:00 ሰዓት፤ ምእራፍ ሁለትን ለማቅረብ 4:00 ሰዓት እንዲሁም ምእራፍ ሶስትን ለማቅረብ 4:00 ሰዓት ተመድቧል።

- ### የሞጁሉ ምዕራፎች

የዚህን ስልጠና አጠቃላይ ዓለማ ከግብ ለማድረስ ሞጁሉ በተለያዩ ምዕራፎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡ ፡ **ምዕራፍ አንድ** ፡ የሙስና ወንጀል ምንነት፤ **ምዕራፍ ሁለት** ፡ የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት፤**ምዕራፍ ሶስት** ፡ በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ፤**ምዕራፍ አራት፡** በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች፤ እንዲሁም **ምዕራፍ አምስት፡** በባህል እና ስፖርት

ዘርፍ የሚፈጸሙ የሙስና ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶች የሚሉ ርእሶችን የያዙ ናቸው፡፡

## ➢ የባህል እና ስፖርት ዘርፍ አጠቃላይ መረጃ

አንድን ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያለውን ተጋላጭነት ለይቶ ትክክለኛዉን የመከላከያ ስልት ለመተግበር የዘርፉን ልዩ ባህሪ በደንብ መረዳት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ለዚህ የዘርፍ ተኮር ስልጠና ዳራዊ መረጃ እንዲሆን የባህል እና ስፖርት ዘርፍ አጠቃላይ መረጃ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ለአንድን ዘርፍ ዉጤት መለኪያነት መነሻ የሚሆነዉ ዘርፉ የተቋቋመበት ዓላማ ወይም የተሰጡት ተልዕኮዎች ወይም ተግባራት ናቸው፡፡ የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 መሰረት የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር፡-

1. ባህልና ስፖርትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ሕጎችን ይቀርጻል፤ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ- ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች እና ሀገር በቀል እውቀቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል፤
3. የባህል ዘርፉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
4. የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ የፈጠራ ችሎታዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የሀገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤
5. በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
6. ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ሥራዎችን ያከናውናል፤
7. በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤
8. የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ እንዲለሙ፣ ሥነ-ጽሑፎቻቸው

እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

9. የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ እውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ሥራዎችን ያከናውናል፣ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤
10. የባህል፣ የስፖርትና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፤
11. ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉም እና በባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤
12. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤
13. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ሕክምና አገልግሎት ያደራጃል፣ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና እፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
14. የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ የስፖርት ማህበራት ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ የሚውል ገቢ ማመንጨት እንዲችሉ ከዓላማቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሥራዎች እንዲያከናውኑ ይፈቅዳል፤
15. የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤
16. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ከውጪ የሚገቡበትንም ሁኔታ ያመቻቻል፤
17. ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ብሔራዊ ስፖርት ልማት ፈንድ በሕግ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፤
18. የስፖርት ፋሲሊቲዎች የሚተዳደሩበትን ስልት ይቀይሳል፤
19. የአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከልን ጨምሮ ሌሎች የስፖርት ማዕከላት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ሥር በማደራጀት በአግባቡ መመራታቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

### ➢ ተተኳሪ ሰልጣኞች

ይህ ሞጁል በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ዘርፍ ስር የሚገኙ ተተኳሪ ሰልጣኞችን ለማሰልጠን የተዘጋጀ ነው፡፡ እነዚህም፡-የዋናዉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ፣ የብሄራዊ ቤተ-መዛግብት እና ቤተመጻሕፍት፣የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ፣የብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር አመራሮች አና ሰራተኞች ናቸው፡፡

### ➢ የማሰልጠኛ ዘዴዎች

ሥልጠናው በሚከተሉት ዘዴዎች የሚቀርብ ይሆናል፡፡ እነዚህም የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣አጫጭር ገለጻዎች፣አስረጂ ናሙናዎችን ማቅረብ፣ጥያቄና መልስ፣የቡድን ዉይይት እና የማጠቃለያ ግብረመልስ መስጠት ናቸው፡፡

### ➢ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች

የሞጁሉን ይዘቶች ለሰልጣኞች በሚገባ ለማቅረብ የሚከተሉት መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህም፤ለባህል እና ስፖርት ዘርፍ የተዘጋጀው ሞጁል እና ፓዎር ፖይንት፣ የላፕቶፕ ኮምፒዉተር፤ LCD ፕሮጀክተር፤ማርከር፤ፍሊፕ ቻርት፤ማስታወሻ ደብተር እና እስክሪፕቶ ናቸው፡፡

### ➢ የመገምገምያ ዘዴዎች

በዚህ ሞጁል ይዘቶች ስልጠና የሚከተሉት መገምገሚያ ዘዴዎች የሰልጣኞችን የቀደመ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ሁኔታ ለመለየት፣ እንዲሁም በስልጠናው ሂደትና ድህረ ስልጠና ያመጡትን የእዉቀት፣የክህሎትና የአመለካከት ለዉጥ ለመመዘን ያገለግላሉ፡፡ እነዚህም፤ቅድመ ስልጠና መጠይቅ፤የቡድን ውይይት ጥያቄዎች፤የግል መገምገሚያ ቼክሊስት እና እንደዚሁም የድህረ ስልጠና አጠቃላይ ምዘና የሚሉት ናቸው፡፡

### ➢ የሞጁሉ አጠቃቀም

ይህንን ሞጁል በሚገባ ለመጠቀም የሚከተሉትን ነጥቦች መከተል አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ሞጁል በአምስት ምዕራፎች የተከፋፈሉ ዋና ዋና ይዘቶች የቀረቡ ሲሆን፤ ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ይዘት ሰልጣኞች የሚጨብጡትን እዉቀት፣ክህሎት እና የሚያሰዩትን የአመለካከት ለውጥ ለመለካት

የሚረዱና በሞጁሉ አጠቃለይ ዓላማ ላይ የተመረኮዙ ዝርዝር ዓላማዎች ተቀምጠዋል፡፡በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ እና መካክል ላይ ስልጠናው አሳታፊ እንዲሆን የሚረዱና የዘርፉ ሰልጣኞች ይዘቱን በሚመለከት ያላቸውን ተጨባጭ ተሞክሮዎች እንዲያካፍሉ የሚያስችሉ የተመረጡ የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣ የግል መልመጃዎች እና የቡድን ውይይት ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ በሁሉም ምዕራፎች ስር ይዘቶቹን የሚያስረዱ አጫጭር ማስታወሻዎች እና ምሳሌዎች እንዲሁም የማሳያ ናሙናዎች ተካተዋል፡፡ በየምዕራፎቹ መጨረሻ ላይ ማጠቃላያ ሀሳቦች እና የማጠቃለያ ጥያቄዎች ቀርቧል፡፡

በሞጁሉ መጨረሻ ላይ ለዚህ ሞጁል ዝግጅት ያገለገሉ መጻህፍት፣ የጥናት ሪፓርቶች፣ ጽሁፎች እና ልዩ ልዩ የማጣቀሻ ምንጮች ተዘርዝረዋል፡፡ በሰልጣኞች የሚሞላ የቅድመ ስልጠና ዳሰሳ መጠይቅ (**በአባሪ አንድ**)፤ እንዲሁም ሰልጣኞች የቀረቡትን ይዘቶች በተመለከተ ምን ያህል እውቀት እንደጨበጡ፣ የትኛውን ክህሎት እንዳዳበሩ እና የትኛው ጽንሰ-ሀሳብ ላይ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት እንደረዳቸው ለማረጋገጥ የራስ መገምገሚያ ቼክሊስት (**በአባሪ ሁለት**) እንዲሁም ለሰልጣኞች የሚሆን የሙስና ተጋላጭነት ልየታ መለማመጃ (**በአባሪ ሶስት**) በቅደም ተከተል ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡

# ምእራፍ አንድ፡- የሙስና ወንጀል ምንነት



## ➢ የምዕራፍ አንድ መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ በዚህ ምእራፍ ስር የሙስና ወንጀል ምንነት፣ የሙስና ዓይነቶች፣ የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያት እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች የሚሉት ዋና ዋና ርዕሶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡



## ➢ የምዕራፍ አንድ ዝርዝር ዓላማ

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኂላ ሰልጣኞች፡-

- ❑ የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
- ❑ የሙስና ዓይነቶችን ያብራራሉ፤
- ❑ የሙስና  ልዩ ባህሪያትን ይገልጻሉ፤እንዲሁም
- ❑ በሀገራችን የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎችን ይዘረዝራሉ፡፡

## ➢ የተመደበው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት ነው፡፡

## ➢ የማነቃቂያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤</u>

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቋቸው የሙስና ወንጀል ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው ሲባል ደረቅ ወንጀል ከሆነው ስርቆት በምን በምን ይለያል?
3. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያት ምን ምን ናቸው?

## 1.1 የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና በእንግሊዝኛ "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ እስካሁን ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመሰጠት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአውሮፓ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን እንዲሁም የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀል ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሰጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን በመዘርዘር ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2 (1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

> *የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣ በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል፡፡*

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *"… የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች*

*ይጨምራል…*" በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎች መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እንደዚሁም በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች፣ በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት የወጣዉ አዋጅ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

## 1.2. የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption)፣ ሲስተሚክ (state capture) እና ፖለቲካዊ ሙስና (Poletical corruption) ተብሎ ይከፈላል፡፡

### 1.2.1 ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና

ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

### 1.2.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሻሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 “ ከባድ የሙስና ወንጀል” ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

### 1.2.3 ስርዓታዊ ሙስና (Systemic capture)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡ ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (Systemic capture) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (State capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 1.2.4 ፖለቲካዊ ሙስና (Political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ

ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዱሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው።

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው። በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው።

## 1.3. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ ሆነ ወንጀል። የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ። የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፤

### 1.3.1 ከወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት አንጻር

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ። በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ። የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል።

### 1.3.2 የሙስና ወንጀል ከሚስከትለዉ ጉዳት አንፃር

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል ። ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች

መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል። ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል። ዜጎች የሚገባቸዉ ልማትና መሠረታዊ አገልግሎቶች በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል። በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል።

## 1.3.3 ከወንጀል ፈጻሚዎች አቅም አንፃር

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው። እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው። ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው።

በሙስና ተግባር ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰቦች የመወሰን አቅም እና ሥልጣን ስላላቸው ምርመራ እንዳይካሄድ በማደናቀፍ ሂደቱን እንዲዘገይ ምርመራው ቢካሄድም ልፍስፍስ እንዲሆን በማድረግ የተጠርጣሪዎችን የተጠያቂነት ደረጃ በማሳነስ ወይም ነጻ እንዲወጡ በማድረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። የተጀመረ ምርመራ እንዲቋረጥ ማድረግ ሲሳናቸው ደግሞ መርማሪውንም ሆነ ከምርመራው ጋር ግንኙት ያላቸውን ግለሰቦች በተለያየ መንገድ ያጠቃሉ።

በሀገራችን በሙስና የተዘፈቀ ሰው እንደብልጥና ቀልጣፋ ሲደነቅ ይስተዋላል። “ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል” ምሳሌያዊ አባባሎች ሙስናን እንደ ነውር ሳይሆን እንደብልጥነት፣ በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ተቀጥሮ ቅንና ታማኝ መሆን እንደሞኝነትና ስልጡን አለመሆን የሚታይ እንደሆነ የሚያመለክቱና ሙስናን የሚያበረታቱ አባባሎች ናቸው። ስለዚህ በየትኛውም የማህብረሰብ ባህል ሌብነት ነውር መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ እሴቶችን በማጉላት በሁሉ ወቀት እየተስተዋለ ያለውን የተዛባ አመለካካት በማቃናት የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ትልቅ ስራ ይጠብቅበታል።

### 1.3.4 በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ ካለመኖሩ አንፃር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

"የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም" የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.3.5 ድንበር ተሻጋሪ ከመሆኑ አንፃር

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሸጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኮን ሊጊሊግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

እንደዚሁም የሙስና ባህሪያትን ከሚከሰትበት ሁኔታና ከውስብስብነት አንጻር መረዳትን ይጠይቃል፡፡

**ከሚከሰትበት ሁኔታ አንፃር**

- በተለያዩ ዘርፎች የሚከሰት (Multi-Sectoral) ነው፡፡ በልማት እና በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ወዘተ ይፈጸማል፡፡
- በተለያዩ የላፊነት ደረጃዎች በሚገኙ ሰዎችና በሌሎች/የመንግስት ሠራተኞች ባልሆኑ ግለሰቦች (Multi-Level) የሚፈጸም ነው፣
- በተለያዩ መንገዶች የሚከሰት (Manifasted in many ways) ነው:: ይህም በከፍተኛ ሙስና (grand)፣ በዝቅተኛ (petty)፣ተቋማዊ (institutional)፣በግለሰብ ደረጃ (individual)፣ ግለሰቦች ተደራጅተው (organized) እንዲሁም ሳይደራጁ (disorganized) በተለያየ መንገድ እና መጠን የሚፈጸም መሆኑ፡
- እየረቀቀ ከመሄዱ አንጻር አንዳንዴ የሙስና ወንጀል ተዋናዮች በአካል የማይተዋወቁ መሆናቸው ፡፡

**ከአፈጻጸም ውስብስብነት አንፃር**

- የአፈፃፀሙ ሂደትና ሥልት ውስብስብ መሆን፣
- በአብዛኛው ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ አለመኖርና ተጎጂው ግለሰብ ብቻ አለመሆን፣
- የፈፃሚዎቹ ማንነት ከተለያየ የመደበቂያ ጎሬ ጋር የመገናኘት ሁኔታ ፣
- በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደ ነውር አለመታየቱና እንደ ጀብድ መቆጠሩ፡፤
- ሙስናን በመዋጋት ተግባር ላይ የተሠማሩትን ጭራሽ የማሸማቀቅ፣ የማሳደድና የማጥቃት ሁኔታ መኖር

በሁሉም ዘርፍ የሚስተዋለው የሙስና ውንጀል ምክንያቶች ብልሹ አሰራሮች እና የሥነምግባር ጉድለቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የተሰናሰለ ሂድት ያላቸው በመሆኑ ለሙስና ውንጀል መበራከት ምክንያት የሆኑትን  የሥነምግባር ጉድለቶች እና ብልሹ አሰራሮችን መቀነስና ሰንሰለቱን መባጣጣስ ሙስናን በመከላከል ሂደት ዋነኞቹ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮች ናቸው ፡፡

## 1.4. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### 1.4.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.4.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.4.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም ፦ የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.4.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

## 1.4.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡ ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

## 1.4.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

## 1.4.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ያለዉ

ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኂላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው  የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.16 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ  እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.4.17 ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡ ፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ  ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.4.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.4.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.4.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.4.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል፡፡

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

### 1.4.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.4.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም።

### 1.4.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረጉም ሆነ ባለማድረጉ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ።

### 1.4.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

- **የማጠቃለያ ጥያቄዎች**

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።</u>

1. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ።

3. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል” ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡
4. በቋማት ውስጥ የግዢ ክፍል ሀላፊ እና ባለሞያዎች፣ ከግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ፣ ግዢዉን የሚፈቅደው ሀላፊ፣የሚረከበው የንብረት ክፍል ሰራተኛ፣ የፋይናንስ ክፍል ሀላፊ፣ ከአቅራቢ ነጋዴ ጋር ተደራጅተው በመመሳጠር የህዝብ ገንዘብ እንዲመዘበር አድረገዉ እራሳችውን እና ነጋዴዎችን ሊጠቅሙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ድርጊት የሚሳተፉት በቡድን ተደራጅተው የተወሰኑ ሰዎች እንጂ ሁሉም ሰራተኞች አይደሉም፡፡ ለመሆኑ በድርጊቱ ውስጥ የእነዚህ ግለሰቦች ድርሻ ምን ሰለሆነ የጥቅም ተጋሪ ለመሆን ቻሉ?

### ➢ የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ያለው ተጋላጭነት



## ➢ የምዕራፍ ሁለት መግቢያ

በምዕራፍ ሁለት ስር አጠቃላይ የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ለሙስና ወንጀሎች ያለውን ተጋላጭነት የሚዳስሱ ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ የፌዴራል ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሚያዚያ 2015 ዓ.ም ባቀረበው የጥናት ሪፖርት ዘርፉ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለው ስለመሆኑ ግኝቶች ቀርበው ነበር፡፡ በተለይም ከግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻፀም፣ ከፋይናንስ አስተዳደር፣ ከተቋም አደረጃጀት፣ ከኦዲትና ቁጥጥር መላላት እና አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን በአግባቡ አለመተግበር ጋር የተያያዙ ስለመሆናቸው ማሳያ ግኝቶች ቀርበውበታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ስር የዘርፉን ተጋላጭነት የሚዳስሱ አጫጭር ይዘቶች የሚገኙ ሲሆን ማሳያ ኬዞችም ተካተዋል፡፡ በሰልጣኞች የሚሰሩ የተሳተፎ ጥያቄዎችም የተሰጡ ሲሆን በመጨረሻም የምእራፍ ሁለት ማጠቃለያ ሳብ ቀርቧል፡፡



## ➢ የምዕራፍ ሁለት ዝርዝር ዓላማዎች

ከምዕራፍ ሁለት ይዘቶች ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

- ✓ በባህልና ስፖርት ዘርፍ የሚታዩ የሙስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የተቋማዊ ብልሹ እሰራሮች ተግዳሮትነትና መንስኤዎችን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ በዘርፉ የሚከስቱ የስነምግባር ጉድላቶች፣ ብልሹ አሰራሮች እና የሙስና ወንጀሎች ጎለተው የሚታዩባቸውን አሁናዊ መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ✓ የኢትዮጵያ ባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ዋናዉ መስሪያ ቤት፣ የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጽሐፍት አጋልግሎት፣ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ የኢትዮጵያ ፀረ-አባረታች ቅመሞች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር ለሙስና ያለዉን አሁናዊ ተጋላችጭነት ይገመግማሉ፡፡

## ➢ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ፡

የምዕራፍ ሁለትን ይዘቶች ለማቅረብ የተመደበው ጊዜ 4፤00 ሰዓት ነው፡፡

## ➢ የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ መልሶቻችሁን ሰርታችሁ በሚሰጣችሁ እድል መሰረት ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. የሙስና ወንጀል ተጋላጭነት መንስኤዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
2. እስካሁን ካላችሁ ምልከታ በመነሳት የኢትዮጵያ ባህል እና ስፖርት ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያለው ተጋላጭነት ምን ይመስላል?

## 2.1 የዘርፉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት አጠቃላይ መረጃ

በተቋማት ውስጥ የስራ ሥነምግባርን አለማክበር፤ ስግብግብነት፤ በአቁራጭ የመክበር ፍላጎት፤ አታላይነት፣ የስራ ሰኣት አለማክበር፣ አቅዶ እዉነትን ማዛባት፣አለመታመን ለብልሹ አሰራሮች መንገድ ይከፍታሉ። ብልሹ አሰራሮች ደግሞ መመሪያን በመጣስ ፣ ሀሰተኛ ሰንድ በመጠቀም፤ ህግ ባለማክበር ፣ ረጅም የስራ ሂደትን በመፍጠር ፣የተቀመጠን ቴክኖሎጂ ባለመጠቀም፣ የቁጥጥር ስርኣትን በማላላት ፣ የግዢ ስርዓትን በመጣስ፣ ንብረትን በአግባቡ ባለመያዝ ፣ የክፍያ ስርዓትን ባለመከተል ፣ ሰነዶችን ባለማደራጀት ፣ወዘተ የሚገለጹ ናቸዉ። እነዚህ የሥነምግባር ጉድለቶች እና ብልሹ አሰራሮች ደግሞ የሙስና ተጋላጭነት መንስኤዎች ይሆናሉ፡
፡

የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ብዙ ገንዘብና የሰው ሃብት የሚያንቀሳቅስበት ዘርፍ ነው። በይዘትም ሀገራዊ አህጉራዊ እና ዓለምአቀፋዊ መገለጫዎች አሉት። ይህም ለሙስና ተጋለጭ ያደርገዋል። በባህል ዘርፍ የሚታየው የሙስና ክስተት የስራ ሂደቱ የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ መወጣት አለመቻል ጋር ይያያዛል። በተለይ ጎጂ አመለካከቶችን በማስቀረት ረገድ የኪነጥበብ፣ ስነጥበብ እና የባህል ልማት ስራዎች በአግባቡ ስራ ላይ ባለመዋላቸው አሁን ያለውን የሙስና ችግር በመቀነስ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ መወጣት አልቻሉም።

ከባህል ጋር ተያይዞ በሕገ-ወጥ መንገድ ቅርሶችን እና ቁሳቁሶችን ከአንድ አገር ወደ ሌላኛው በቀላሉ ለማውጣት እና ለማጓጓዝ አስቻይ ሁኔታ እየፈጠረ በመሆኑ ስቆርቆቱን በማባባስ የቴክኖሎጂ እድገት የራሱን ተጽእኖ እያሳደረ ነው። በመሆኑም በቅርስ ስርቆት መንገድ የሚፈፀሙ ሙስናዎች መከላከል ካልተቻለ ከታሪኮች እና ቅከርሳቅርሶች

የሚያገኘውን ጥቅም ከማስቀረት በተጨማሪ በማንነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል (Dalena, 2016)፡፡

ሌላኛው ሙስና ከሚስተዋልባቸው የባህል ዘርፎች ወስጥ ሚዲያና የመዝናኛው ኢንዳስትሪ ነው፡፡ የመገናኛ ብዙሃን እና የመዝናኛ በባህሪው በጣም ከፍተኛ የገበያ ውድድር የሚስተዋልበት መሆኑ ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡ በተለይ የፊልም ኢንዳስትሪ ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ ዘርፎች ዋናኛው ነው፡፡ የተፋጠነ የፊልም ቀረፃ ለማካሄድ፣ ምቹ የቀረፃ ቦታ ለማግኘት፣ የአገር ውስጥ ፊልም ሠራተኞች ጋር መልካም ግኑኝነት ለመፍጠር እና አስፈላጊ የቀረፃ እቃዎች ለማጓጓዝ ክፍየዎች የመፈፀም ተግባር ውስጥ ይገባሉ፡፡ በተለይ ከአገር ውጭ የሚደረጉ ቀረፃዎች ይህ ዓይነት ሙስና ይስተዋልባቸዋል (Siegel,2016 )፡፡

በተጨማሪም United Nations Office on Drugs and Crime (2021) ባደረገው ጥናት የሚከተሉትን በስፖርት ዙሪያ የሚከሰቱ መስናዎችን የተደራጁ ወንጀለኞች የሚሳተፉበት፤ የቁማር ውርርድ ድርጅቶች የሚሳተፉበት፤ የስፖርት ውድድሮች ማጨበርበር፤ ውድድር ማዘጋጀት ምርጫን ማዛባት፤ የመገናኛ ብዙሃን የስፖርት ዘገባ ስርጭት እና ስፖርት አመራሮቸ ብልሹ አሰራር ጋር የሚገናኙ ናቸው በማለት በማለት አስፍሯል፡፡

**ምሳሌ 1**፡ የሚከተሉት በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር የሥነ-ምግባር መከታተያ የቀረቡ የ2016 ዓ.ም የዘርፉን ተጋላጭነት ሁኔታ የሚያሳዩ ሪፖርቶች ናቸው፡፡

- *የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋል አለመቻል፤*
- *ተቋማዊ የሰራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያዎችን ተግባራዊ የማድረግ ክፍተትና የድጋፍ፤ክትትልና ግምገማ ስርዓት ደካማ መሆን፤*
- *አገልግሎትን በስታንዳርድ መሠረት መስጠት የሚያስችሉ ተቋማዊ የዜጎች ቻርተርን አፈጻጸምን የመከታተል፤ የመደገፍ እና የመገምገም ስራ ደካማ መሆን፤*
- *በመንግስት ንብረት አያያዝ፣አጠባበቅ፣ አጠቃቀም እና አወጋገድ ዙሪያ ያሉ ህጎችና የአፈፃፀም መመሪያዎቸን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ክፍተት መኖር፤*

*(ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ የ2016 ዓ.ም የሥነ*

ምግባር መከታተያ ስራ አስፈጻሚ የ 12 ወር ሪፖርት)

## 2.2. የዘርፉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት መንስኤዎች

### 2.2.1 የተቋማት አደረጃጀት ክፍተት

በሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት መሰረት በዘርፉ የሚገኙ የሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም የጋራ ትንተና ለማካሄድ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ አለመወጣታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

የየተቋማቱ የሕግ ክፍሎች ራሳቸውን ችለው ቢደራጁም በሁሉም በሚባል ደረጃ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥባቸው አሠራር ስለመኖሩ መረጃ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም በአብዛኛዎቹ በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት አለመሰጠቱ የመንግስትን ጥቅም ሊጎዳ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል (ኮሚሽን, 2015)፡፡ ስለዚህ በዘርፉ ስር የሚገኙ ክፍሎች ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት እንደየ አስፈላጊነታቸው አንድ ላይ መቀናጀት ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.2.2 የተጠያቂነት አለመስፈን

ተጠያቂነት አንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት ጋር በተያያዘ አፈፃፀሙን በመገምገም ለሚፈጠሩ ጉድለቶችና ጥፋቶች ኃላፊነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በተለይ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ መንግስታዊ ተቋማት የሚያስተዳድሩትን የህዝብ ሀብት በተገቢው መንገድ ለህዝብ አገልግሎት የማዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩም አስፋላጊውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ የህዝብ ሀብት እንዳይባክንና የመንግስት ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የተሰጣቸውን ስልጣን አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳያውሉ የማረጋገጥ ስራ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በባህልና

ስፖርት ዘርፍ ስር ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር ተያያዥ ጉዳዮች በኮሚሽኑ ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቦ ይገኛል፡፡

ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር የብሄራዊ ቤተመዛግብት እና ባህልና ስፖርት የስነምግባር ደንብ ያዘጋጁ ሲሆን፤ የቀሩት ሶስቱ ቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) ስለማዘጋጀታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡

በወቅቱ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ አምስት ቅሬታዎች ቀርበው ለአምስቱም ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ባህልና ስፖርት ሚ/ር አራት ቅሬታዎች ቀርበው ለሶስቱ ምላሽ የሰጠ ሲሆን፤ አንዱ በሂደት የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የቀሩት ሶስት ተቋማት ምንም ቅሬታ ያልቀረበላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ብልሹ አሰራሮችና የሙስና ወንጀሎች ከተለዩ ቀጥሎ ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል፡፡



**<u>ምሳሌ</u>**፡ በ2013 በጀት ዓመት በጨረታ ውል ስምምነት የግዥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አቅራቢው ድርጅት ያላቀረባቸው እቃዎች ተጠያቂነት ያልሰፈነበት ሁኔታ መኖሩን ያሳያል፡፡

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | ያንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | የአቅራቢው ድርጅት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሴት  አጭር ቆዳ ጫማ | 128 | 334.17 | 42.773.76 | አቅራቢ 1 |
| 2 | የልብስ ሳሙና 200 ግራም | 10.047 | 12.65 | 127.094.55 | አቅራቢ 2 |
| 3 | የኮምፒውተር ወርቀት | 800 | 119.45 | 95.560.00 | አቅራቢ 3 |
| 4 | ላፕቶፕ የኮምፒውተር ኮር አይ 5 | 5 | 23.020.88 | 115.104.40 | አቅራቢ 4 |
| 5 | እስካነር ፎር ቤዜክኦፎስ ፐርፐዝ | 4 | 12.704.45 | 50.817.80 | አቅራቢ 5 |
| 6 | የፕሪንተር ቶነር 26 ኤ | 10 | 372.00 | 3.720.00 | አቅራቢ 6 |

### 2.2.3. የተቋም ግልፅነት አለመኖር

ተቋማት ራሳቸውን ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ዓላማቸውን ለማሳካትና አፈጻጸማቸውን ለማሳደግ ግልጽነት ሚናው የጎላ ነው። ግልፅነት ሙስናን ለመከላከል ከሚያስችል መሰረታዊ ተግባራት አንዱ ነው። ይህን ለማሳካትም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅና አሳታፊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተቋማዊ ግልጽነት ማለት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥን ያጠቃለለ ነው። ግልፅነትን የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳ መልካም ውጤት ቢመዘገብም ሂደቱ የተአማኒነት እና የቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም። በባህልና ስፖርት ዘርፍ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በኮሚሽኑ ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቦ ይገኛል።

በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር የተገባ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ። ስለሆነም የዕቅድና በጀት ትግበራው የተሳካ እንዲሆን አጋዥ ሚናውን ተጫውቷል ተብሎ ይገመታል። በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የዕቅድ ግምገማ የሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመለየት በሚያስችል መልኩ በጋራ ውይይት የተደረገባቸው መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል። ከተቋማቱ አመራሮች ሰራተኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄዱ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና ብልሹ አሰራሮችን የመለየት ስራ መሰራታቸውን ከቀረቡ ሰነዶች ለመገንዘብ ተችሏል። በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት

ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በግልባጭ እንዲደርሳቸው ከማድረግ ውጪ በብሮሸር፣ በዌብሳይታቸው፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ ተደራሽ ስለማድረጋቸው መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙት ተቋማት ውስጥ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የስራ ሂደቶቹ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚመለከታቸው አካላት የሚሳተፉ መሆናቸውን መረጃ ያቀረቡ ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስቱ ተቋማት መረጃ ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ከፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በስተቀር ሁሉም የግዥና ጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በጋዜጣ እንደሚያስራጩ ቢገልጹም ይህን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ካሉት ተቋማት ውስጥ ከብሄራዊ ቤተ-መዛግብት እና ቤተ-መጻህፍት አገልግሎት በስተቀር የቀሩት ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው በቃል ቢገልጹም ስለማከናወናቸው መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ በማህበራዊ ሚድያ አጠቃቀም በኩል ያለው ልምድ በበጎ የሚታይ ሲሆን ሁሉም ተቋማት በሚባል ደረጃ ማህበራዊ ሚዲያ ኣካውንት ወይም ድህረገጽ እንዳላቸው ከምልከታው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አጥጋቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ አለመሆኑ፣ የበጀት አጠቃቀም መረጃ ለተገልጋይ የማሳወቅ ውስንነቶች፣ በተወሰኑ ተቋማት የሚመለከታቸው አካላትን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ለማሳተፍ አለመቻሉ በውሳኔዎች ተአማኒነት ላይ ጫና ሊያሳድር መቻሉ፣ውሳኔዎች እና ቃለ-ጉባኤዎች ተደራሽ አለመደረጋቸው አስተያየት የመሰብሰብ እድልን ያጠበዋል፣ ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ መሆን ላይ ያሉ ውስንነቶች መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል (የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)፡፡

**<u>ምሳሌ፡</u>**
*የፌ/መንግስት የግዥ/ንብ/አስ/ር/አፈፃፀም ማንዋል አጠቃላይ ድንጋጌዎች 2.(2.2)የግዥ መዝገቦች (ሰነዶች)በማለት ተጠቅሶ ይገኛል፡፡እነዚህ ሰነዶች የሚባሉ ክፍያ የተፈጸመባቸው*

*ሰነዶች፣የግዥ መረጃዎችና የወጪ ደረሰኞች እንዲሁም ልዩልዩ የሂሳብ መዛግብቶች በተደራጀ እና በቀላሉ ማግኘት በሚቻል መልኩ መቀመጥ እና **በአንድ ክፍል ውስጥ በሂሳብ ሰነድ ያዥ ሠራተኛ እጅ ኃላፊነት መጠበቅ እንዳለበት የፋይናንስ አሰራር ያስረዳል**፡፡*

*ሆኖም ግን በተቋሙ ውስጥ የግዥ ሥራ የተፈፀመባው የጨረታ ሰነዶች እና ልዩ ልዩ ስነዶች ማንኛውም መረጃዎች በተለያዩ ቦታዎች የሚቀመጡ መሆናቸው ሰነድ ያዥ ሰራተኛ ቢኖርም ሰነዶች በአግባቡ ተደራጅቶ የሚቀመጡበት ራሱን የቻለ ክፍል የሌለ መሆኑ በጥናቱ ሂደት ለማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት አሰራር ማንኛውም ሰነዶች በቀላሉ እንዳይገኙ እና እንዲጠፉ የሚያደርግ ፣ለክትትልና ለቁጥጥር ሲፈለጉ የማይገኝ ከመሆኑም ባሻገር ለአንዳንድ የማስተካከያ ስራና የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዳይኖር በማደረግ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት ሊፍጥር ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡*

*የመንግስት ሰነዶች በአንድ ክፍል ውስጥ በሂሳብ ሰነድ ያዥ ሠራተኛ እጅ ኃላፊነት መቀመጥ እና ከአደጋ መጠበቅ የሚገባቸው መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ትኩረት ባለመስጠት ስነዶች በተለያዩ ቦታ እንዲቀመጡ ማድረግ ለሙስናና ለብልሽ አሰራር የሚያጋልጥ መሆኑ እንዲሁም የሂሳብ ሰነዶች ለአደጋ እንዲጋለጡ፣እንዲጠፉ፣ እንዲበላሹ የሚያደርግ አሰራር መኖሩን በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

### 2.2.4 አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን አለመተግበር

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ያለባቸውን

ማሻሻል ተገቢ ነው።

**ምሳሌ 1፡**

*የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ ሰኔ2002 ዓ/ም የወጣው የግዥ የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት ክፍል ሁለት ቁ6(10) ሥር በቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ዋና ዋና ገፆች ላይ ማህተም እየተደረገ መፈረሙን ያረጋግጣል፣የጨረታ መክፍቻ ቃለ-ጉባኤ እንዲዝ ያደረጋል በማለት በግልጽ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡*

*በጨረታ እና በዋጋ ማቅረቢያ ሰነዶች ዋና ዋና ገፆች ላይ የሚመለከታቸው የተቋሙ ኃላፊዎች ፊርማ የሌላቸው ማህተም የማደረጉ ሰነዶች መኖራቸውን በምልከታ የታዩ ጉዳይ ነው፡፡ተወዳዳሪዎች ለውድድር የሚያቀረቧቸው የዋጋ ማቅረቢያ እና የጨረታ ግዥ የቴክኒክ የመወዳደረያ ሃሳብ በጨረታ ኮሚቴ ከተከፈተ ለውድድሩ የሚሰፈልጉ መረጃዎችን መሟላታቸውን ከተረጋገጠ በኋላ የተጫራቾች የመወዳደሪያ ሃሳቦች የቴክኒክ ግምገማውን ለሚሰራ አካል ከመሰጠቱ በፊት በጨረታ ኮሚቴ አባላት በሙሉ ተፈርሞ መያዝ እንዳለበት በግዥ መመሪያው ላይ የተቀመጠ ሲሆን ጨረታ ከተከፈተ በሃላ የተጫራች የመወዳደርያ ሀሣብ ላይ የቴክኒክ ግምገማውን ለሚሰራው አካል ከመሰጠቱ በፊት በጨረታ ኮሚቴ አባላት በሙሉ የማይፈረም መሆኑ እንዲሁም የተቋሙ ማህተም የሌላቸው ወይም የማይደረግ መኖሩን፣ተከታታይነት ያላቸው ቁጥሮች የማሰጥ እንደሆነ ከቀረበልን ሰነዶች ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ የአሰራር ክፍተት ደግሞ ሊፍጥር የሚችለው በጨረታ ወቅት ተገቢው መረጃ አያይዘው ያቀረቡትን ተጫራቾች ሰነድ ማውጣት ይችላል፣እንዳያሸንፎ ለማድረግ እድል ሊፍጥር ይችላል፣ የጨረታ ሰነድ ሲከፈት ያልተገኙ ተጫራቾች የሰነድ ማሰረጃ በማስገባት የተሻለ ነጥብ እንዲያገኙ የሚያስችል ሂደት አለው ተብሎ ይገመታል፡፡ይህ ለሙስናና ብልሹ አሰራር እድል ሊፍጥር ይችላል፡፡*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

**<u>ምሳሌ 2፡</u>**

*የሰራተኞች የአደጋ መከላከያና መቆጣጠርያ ደንብ ልብሰ መመሪያ ላይ የቫዚሊን አቅርቦት ለየትኛውም የስራ ክፍል እንዲኖር ባልተፈቀደ ሆኔታ 1480 በካርቶን … አሸናፊ ድርጀት ከቫት ጋር በብር 200.000 ጠቅላላ ዋጋ በብር 296.00 ብር የአንዴ ግዥ ብቻ ሲሆን የተቋሙ መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ ግዥ የተፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በመሆኑም ይህ አሰራር የመንግስት ገንዘብ ለብክነት የዳረገ ሲሆን ለሙስናና ለብልሹ አሰራር ክፍተት የፈጠረ ነው።*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

**<u>ለምሳሌ 3</u>**፡ ያለአግባብ ክፍያ መፈጸም፡-

- የካቲት /2012 የወጣዉን የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 3 በመጣሥ በሀረር ከተማ ለተካሔደው ኮንፍራንስ ለ 60 ሰዎች የተከፈለ የዉሎ አበል፡፡ *በሁለት ቀን አበል 53084.00 መከፈል ሲገባው በቀን 20/4/15 በወጪ ማመሳከሪያ ቁጥር 00027988 ብር 137560.00 በወጪ ማመሳከሪየ ቁጥር 00027989 ብር 127860.00 በድምሩ 265560.00 በመክፈል ያለአግባብ በብልጫ ብር 212336.00 ወጪ ሆኗል።*

- በሚዛን አማን ከተማ ለተከናወነው ፌስትቫል ለአልጋ ለሪፍሬሽመንት የተከፈለ ክፍያ ኦዲት ሪፖርት፡-

  *የካቲት 26/2015 እስከ መጋቢት 3/2015 ዓም በሚዛን አማን ከተማ በተካሄደው የስፖርተ ፌስቲቫል ለአልጋና ሬፍሬሽመንት በወጪ ማመሳከሪያ ቁጥር 00028661 ብር 290600.00 ለሆቴል ክፍያ ሲፈጸም የተሳታፊዎች ዝርዝር ያልቀረበና የሚመለከተው አካል ክፍያዉን ስለመፍቀዱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ*

## 2.2.5 የንብረት አስተዳደር ጉድለት

የአንድ ንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ ይህ የተገዙ ንብረቶች መረከብን፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅን፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን በክትትል ሪፖርት የተገኘዉ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡



**ምሳሌ፡**

*ወቅታዊ የንብረት ቆጠራ አለማድረግ በንብረት አስተዳደር ላይ የሚደረግ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በማላላት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ በ2014 ብሄራዊ ቤተመዛግብት ብር 186,969 የሚያወጡ የተለያዩ ቆርቆሮዎችን በሽያጭ ያስወገደ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ብር 203,760 የሚያወጡ ብዛታቸው 33 የሆኑ የተለያዩ ስፖርት ዕቃዎችን በስጦታ ያስተላለፋቸው ንብረቶች መሆናቸውን ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የቀሩት ሶስት ተቋማት ምንም አይነት የንብረት ማስወገድ ስለማካሄዳቸው መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ በስፖርት አካዳሚ፤ በፀረ-አበረታች እና ብሄራዊ ቤተመዛግብት የሚወገዱ ንብረቶች ተገቢው ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገላቸው ሲሆን፤ በቀሩት ሁለት ተቋማት ግን ጥበቃና አያያዝ ስርዓቱ በቂ እንዳልሆነ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ንብረቶች ለጉዳት ወይም ለስርቆት የተጋለጡ እንዲሆኑ*

*በማድረግ የመንግስት ሀብት ሊባክን የሚችልበትን ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

### 2.2.6 የግዥ ስርአትን አለመከተል

ድርጅቶች ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለማሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ በዘርፉ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ሪፖርት የሚከተለውን ይመስል ፡፡

**<u>ምሳሌ፡</u>***በብሄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመፃህፍት የገንዘብ መጠናቸው ከ2.7 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆኑ በዋጋ ማቅረቢያ፣ ከ2.6 ሚሊዮን ብር በላይ በውስን ጨረታ፣ 555,386 ብር በቀጥታ የግዥ ዘዴ ከአንድ አቅራቢ የተከናወኑ ግዥዎች መኖራቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የብር መጠኑ 262 ሺህ የሚሆን የግዥ ሂደት ላይ ደግሞ የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦበት እንደተሰረዘ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ብሔራዊ ቴያትር 5.7 ሚሊዮን ብር በላይ በፕሮፎርማ ግዥ ዘዴን በመጠቀም ግዥ የተፈፀመ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

### 2.2.7. የሰው ሀብት አስተዳደር ክፍተት

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መስረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያለው የሰው ሀብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ኃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ዘርፉን በተመለከተ የሚከተሉት ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ የቅጥር መመሪያን ተግባራዊ በማድረግ ከአድሎ፣ከጉቦ፤ ከትውውቅ፣ ከዝምድና አሰራር ነጻ የሆነ የቅጥር፣ የዝውውር እና እድገት እንዲሁም የስልጠና እድል አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

**<u>ምሳሌ፡</u>**

*የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እና የስራ ልምድ ማጣራትን በተመለከተ በሁሉም*

*የዘርፉ ተቋማት ስለመስራታቸው መረጃዎች አልቀረቡም።*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

## 2.2.8. የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ተግባርን በአግባቡ አለመከናወን

የአገሪቱ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ህግ በሚደነግገው መሰረት የፌዴራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ሀብታቸውን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው። ተቋማትም ቅጥር ከመፈፀማቸው በፊት የመጀመሪያ ወይም ዳግም ምዝገባ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ሥርዓት የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ምንጫቸው ያልታወቀ (ተገቢ ያልሆኑ) ንብረቶችን ለመለየት ፋይዳው የጎላ ነው።

**ም ሳ ሌ ፡**

*በወቅቱ በብሔራዊ ፀረ አበረታች እና ብሔራዊ ቲያትር ሀብት ምዝገባ ስራ ለመጀመራቸው መረጃ አልቀረበም። የቀሩት ሦስቱ ተቋማት የአመራር እና የሰራተኛ ሀብት ምዝገባ መረጃ እንሚያሳየው ማስመዝገብ ካለባቸው ባህልና ስፖርት ሚ/ር 5 አመራሮች ማስመዝገባቸውን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፣ እንዲሁም ከ330 ሠራተኞች መካከል ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ ያስመዘገቡት 39 ብቻ ናቸው። የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ማስመዝገብ ከሚገባቸው 4 አመራሮች አራቱም አስመዝግበዋል። እንዲሁም ከ178 ሠራተኞች መካከል 150 አስመዝግበዋል። ብሔራዊ ቤተ መዛግብት ማስመዝገብ ከሚጠበቅባቸው 12 አመራሮች 2 ብቻ አስመዝግበዋል። እንዲሁም ከ318 ሠራተኞች መካከል 45 ብቻ እንዳስመዘገቡ መረጃዎች ያሳያሉ። በአጠቃላይ በዘርፉ ማስመዝገብ የሚጠበቅባቸው አመራሮች 21 ሲሆኑ ያስመዘገቡት 6 (28%) ብቻ ናቸው። ሰራተኞችን በተመለከተ 826 ሲሆኑ ሀብት ያስመዘገቡት 234 (28%) ሰራተኞች ናቸው።*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

## 2.2.9. የኦዲት እና ቁጥጥር ሪፖረት አለማስተካከል

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ

የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የውጭ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡ ፡ በባህልና ስፖርት ዘርፍ መስሪያ ቤቶች የኦዲት አስተዳደር ስርአት ላይ በ2015 ጥናት የተከናወነ ሲሆን የነበረው የኦዲት ግኝት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ምሳሌ 1**

- *በብሄራዊ ቤተመዛግብት 1.2 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ፣*
- *በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ከ2.2 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተሰበሰበ እና ከ1.5 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተከፈለ ሂሳብ መኖሩ*
- *በብሄራዊ ትያትር ቤት 1.4 ሚሊዬን ብር ለማን እንደሚከፈል እና እንደተከፈለ የማይታወቅ ገንዘብ በኦዲት ግኝት መኖር፤በፍርድቤት ውሳኔ የቀድሞ ቴያትር ቤት ዳይሬክቴሩ 196896.50 ብር እንዲከፍሉ የተወሰነ ቢሆንም እስካሁን ድረስ እንዳልተሰበሰበ ግኝቱ ያሳያል፡*

*(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*


**ምሳሌ 2**፡

- *በሂሳብ መደብ 5217110 የተያዘ የግዢ ቅድመ ክፍያ ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት የቆየ ብር 9911796.88*
- *ሌሎች ተመሳሳይ ግኝቶች በድምሩ 19750164.53 ብር ግኝት ተመዝግቧል፡፡ (ፌዴራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝት ሪፖርት፣ 2016)*

### 2.2.10 የግንባታ የፕሮጀክቶች አስተዳደር ጉድለት

በባህልና ስፖርት ዘርፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የምርምር ፤ የእድሳትና

ጥገና ፤የግንባታ የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡



የአደይ አበባ አለም አቀፍ ስታዲየም ግንባታ ፕሮጄክት

**<u>ለምሳሌ</u>** ፡ ኢንፍራስትራክቸር ትራንስፓራንሲ ኢንሼቲቭ ኢትዮጵያ ሪፖርት 2016 የአደይ አበባ ስታዲየም ግንባታ ፕሮጀክት በተመለከተ

- *የሁለተኛ ዙር ጫረታ ሂደት የጫረታ ህግን ያልተከተለ እና ተኣማኒነት ያልነበረው መሆኑ፤*
- *የጫረታዉ መፈራረም ሂደት ረዥም ጊዜ የወሰደ መሆኑ፤*
- *የፕሮጀክቱ ግንባታ አፈጻጸምና የወሰደው ጊዜ አለመጣጣም፤*
- *የክፍያ መዘግየት፤*
- *የሁለተኛ ዙር ግንባታ አፈጠፃፀምን ለመገምገም ከተፈረመው የውል ስምምነት በስተቀር ምንም አይነት የፕሮጀክት ሰነድ አለመገኘቱ፤*

**ምሳሌ**

- *የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የገንዘብ መጠኑ ከ3.3 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን የግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቀና ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆኑ፤ የገንዘብ መጠኑ 16.4 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን የግንባታ ፕሮጀክት የኮንትራት ውል ስምምነት የተቋረጠ መሆኑ፤*
- *የገንብ መጠኑ 21.2 ሚሊዮን በላይ ተቋራጩ የተከሰሰበት ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። በብሔራዊ ቤተመዛግብት የገንዘብ መጠኑ 450 ሚሊየን ብር በጊዜው ያላለቀና የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ። በመሆኑም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ፣ በተደጋጋሚ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው፣ ተጨማሪ ስራ የተሰጠባቸው እና ግዙፍ በጀት ስለሚፈስባቸው የሙስና ስጋት ሊሆኑ ይችላሉ።*

  *(የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት፣ 2015)*

## 2.2.11. የታዳጊ ስፖርት ፕሮጀክቶች ምልመላና አስተዳደራዊ ችግሮች

ከታዳጊ ስፖርት ፕሮጀክቶች ሰልጣኞች ምልመላ እና ስልጠና ጋር በተያያዘ ለብልሹ አሰራር መንስኤ የሚሆኑ ችግሮች እንዳሉ ጥናቶች ያመለክታሉ።

**ምሳሌ**

- ከ2002 ጀምሮ ለአንድ ስፖርተኛ የተመደበዉ የምግብ ወጪ ማነስ ስፖርተኞቹ ለሌሎች ለስነምግባር ጉድለትና ብልሹ አሰራሮች እንዲጋለጡ ምክንያት ሆናል(Samson, Hirko & Asim Khan, 2017).
- የሰልጣኝ እና አሰልጣኝ ጥምርታ አለመጣጣም፤የፊዚዮቴራፒስት እና የስፖርት ሳይኮሎጂስት ባለሙያ እጥረት መኖር ለስልጠና እድል ለማግኘት የሚደረግ ጥረት እና የባለሞያ እጥረት ለስነምግባር ጉድለት ፤ ለብልሹ አሰራር እና ሙስና ምክንያት ይሆናል (Samson, Hirko & Asim Khan, 2017).

## 2.2.12 ከስፖርት ፌዴሬሽኖችና ማህበራት ጋር የተያያዙ ችግሮች

በስፖርት ዘርፍ የሚታዩ ሙስናዎች ሁለት መልክ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የመጀመሪያው መልክ የሚገለፀው ተሳታፊዎች በሚደርጉት መስተጋብር ነው፡፡ አትሌቶች፣ የስፖርት ኃላፊዎች እና ዳኞች ውጤት ለማስቀየር የመደረግ በጉቦ ወይም ውለታ በመቀባበል የሚሳተፉበት ነው፡፡ ሁለተኛው መልክ ስፖርተዊ ሙስና የውድድር ምድቦች፤ ውድድሮች ማስተናገድ እና ስፖርት ሃላፊዎች ምርጫ የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ አገሮች ለመመረጥ ወይም ዜጎቻቸው ለማስመረጥ በሚያደርጉት ጥረት ድምፅ ለመግዛት ሙስናን ጥቅም ላይ ያውሉታል (Hwang, 2016)፡፡ በተጨማሪም ከእግር ኳስ ክለቦች ጋር በተያየዘ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች የስፖርት ዘርፍ ችግሮች ናቸው፡፡

**ምሳሌ፡** የእግር ኳስ ክፍያ እና ዝውውርን በተመከተ የሚታዩ አስተዳደራዊ ክፍተቶች ፡-

- *የእግር ኳስ ደሞዝ የክለቡን 90% በጀት ይይዛል፣ የክለቦች ገቢ እና ወጭያቸው አይመጣጠንም፡፡ ስለዝህ ክለቦ ሊግ ውድድር ላይ መወዳደር ይከብዳቸዋል (Abiy, 2018).*
- *የኢትዮጵያ እግር ኳስ ክለቦች ብዙ በመክፈል ከአፍሪካ 3ኛ ናቸው፣ ግን ከትኬት የሚጋኘው ገቢ ትንሽ ነዉ (Abiy, 2020)፡፡*
- *ብዙ እግር ኳስ ክለቦች ደሞዝን ግዜዉን ጠብቆ ለተጫዋቾች አይከፍሉም (Abiy, 2018)፡፡*

## 2.2.13 ከአበረታች ቅመሞችና መድሃኒቶች መጠቀም ጋር የተያያዘ ችግር

ሌለኛዉ በስፖርት ዘርፍ የሚስተዋለዉ የስነምግባር ችግር ከአበረታች ቅመሞችና መድሃኒቶች መጠቀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አበረታች ቅመሞችን መጠቀም አትሌቶች በተለያየ ጊዜ ቅጣት ተጥሎባቸዋል፡፡

**ምሳሌ፡**

- *አንዲት የኢትዮጵያ አትሌት አበረታች ቅመም በመጠቀሟ ለ5 አመት ከአትሌትክስ ውድድር ተቀጣለች፡፡ (Daniel፣2022).*
- *አንድ የኢትዮጵያ አትሌት አበረታች ቅመሞችን መጠቀሙ ተረጋገጠ (Dawit, 2019)*
- *አንዲት የኢትዮጵያ አትሌት አበረታች ቅመሞችን በመጠቀሟ ከአትሌትክስ ውድድር ታገደች (Fabrice,2016).*

## ➢ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን የቡድን ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልሶቻችሁን በተጠየቀው መሰረት ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡**

1. ከላይ ከተዘረዘሩት የተቋሙ ስልጣንና ተግባራት ውስጥ በአግባቡ እንዳይሳካ የስነምግባር ጉድለት ፤ ብልሹ አሰራሮች እና የሙስና ወንጀሎች የበለጠ አደጋ ችግር የሆኑበት የትኛው እንደሆነ ማሳያዎቹን ጭምር በቡድን ዉይይት በመለየት በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ በደረጃ ተራትራ ቁጥር አስቀምጡ፡፡

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | |
| | | | | | | | | | |

2. የሁሉም ቡድን አባላት መልስ ድምር ዉጤት መሰረት የበለጠ በስነምግባር ፤ በብልሹ አሰራር እና በሙስና ምክንያት ዉጤታማ ያልሆኑ በአዋጅ ለተቋሙ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በደረጃ ማስቀመጥና የችግሮቹን ማሳያዎች ለተሳታፊዎች ግለጹ፡፡

1ኛ____________ 2ኛ ___________ 3ኛ ____________

3. በባህልና ስፖርት ዘርፍ ከሚገኙት ዘርፎች ስር ያሉ የስራ ሂደቶች/ ቢሮዎች ውስጥ የበለጠ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮ የሚጋለጡት የትኞቹ ናቸው? ለምን?

## ➢ የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

የሙስና ወንጀሎች እንዴት በተቋማት የአደረጃጀት፣ በተጠያቂነት አለማስፈን ፤ የተቋማቱ ግልፃዊ አሰረር መጓደል፣ የአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አለመተግበር፣ የንብረት አስተዳደር ችግር፣ የግዥ አስተዳደር ሂደቶች ችግር፣ የሰው ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ችግር፣ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አተገባበር ጉድለት፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር ጉድለት እና ኦዲትና ቁጥጥር መላላት ችግሮች ምክንያት እንዴት እንተከሰቱ ማሳያ ኬዞች ጋር ቀርበዋል፡፡ ዘርፉ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ተጋላጭነት ያለው መሆኑ በተለያዩ ጥናቶች ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ይህም ከግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻፀም፣ ከፋይናንስ አስተዳደር፣ ከተቋም አደረጃጀት፣ ከስፖርት ትጥቅ ጊዢ፣ ከስፖርተኞች ምልመላ እና ስልጠና፣ ከአበረታች ቅመሞች መጠቀም ፤ ከኦዲትና ቁጥጥር መላላት እና አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን በአግባቡ አለመተግበር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሌለኛው አለም አቀፋዊና አሁናዊ ችግር በስፖርት ቤትንግ (ጫወታዎች ሽፋን) የማጭበርበር እና የህገወጥ ቁማር መስፋፋት ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ትልቁ የተጋላጭነት ስጋት ነው፡፡ በኢፌዲሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት ለመፈፀም ሙስና እና ብልሹ

**አሰራሮች እንቅፋት የሆኑባቸውን ዘረፎች የተጋላጭነት ደረጃ በጥናት በደንብ መለየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ ሰራተኞችም ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎችን የመለየትና በተጋላጭነት ጥናት ዉስጥ ለመሳተፍ እዉቀት ሊኖራቸው፣ ክህሎትንም ማደበርና የአመለካከት ለዉጥንም ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡**

# ምዕራፍ ሶስት፡- በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉት ጉዳትና የመከላከያ ስልቶች



## ➢ የምዕራፍ ሶስት መግቢያ

በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች እንደተቋም ብሎም እንደሀገር ከፍተኛ ጉዳቶቸን ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ያለው መተማመን ይሸረሽራል፣ በገንዘብ በሚሰሩ ስራዎች ላይ አለመተማመንን ያመጣል፣ በአትሌቶች እና አሰልጣኞች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያደርሳል፣ የዘርፉን መልካም ስም ያጠለሻል፣ የወጣት አትሌቶች ተሳትፎ መጠን ይቀንሳል፣ የሰራተኞች ተነሳሽነትን ይቀንሳል፣እንዲሁም የመስሪያቤቱን ስራ አፈጻጸም ይጎዳል፡፡ በአጠቃላይ እንደሀገር ዘርፉ ተልዕኮዉን እንዳይወጣ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ስር የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ዘርፍ ተኮር ጉዳቶችን የሚመለከቱ ይዘቶች ከቡድን ዉይይት እና ማጠቃለያ ሀሳቦች እንዲሁም ከራስ መገምገሚያ ቼክሊስት ጋር በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡



## ➢ የምዕራፍ ሶስት ዝርዝር ዓላማዎች

ከምዕራፍ አራት ይዘቶች ስልጠና በኂላ ሰልጣኞች ፦

- ✓ በባህልና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ያሚያስከትሉትን ጉዳቶች ያስረዳሉ፡፡
- ✓ የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- ✓ የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
- ✓ በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶችን ይዘረዝራሉ ፡፡
- ✓ በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ዘርፍ  የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣ እንዲሁም
- ✓ በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ዘርፍ የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፡፡

## ➢ የምዕራፍ ሶስት ይዘቶች ለማቅረብ የተመደበው ጊዜ

በዚህ ምዕራፍ ስር የሚገኙ ይዘቶችን ለማቅረብ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት ነው፡፡

## ➢ የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከራሳችሁ የቀደመ ልምድ በመነሳት መልሶቻቸውን ለተሳታፊዎች በቃል ግለጹ፡፡

1. በባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉት የሚችሉት ጉዳቶች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
2. ብልሹ አሰራሮችን እና ሙስና ወንጀሎችን ለመከላከል የሚረዱ ስልቶች ምን ምን ናቸው?

## 3.1. በባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች

የባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ከራሱ ከተቋሙ አልፎ በሀገር ገጽታ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ የትምህርታዊ እና ሥነ-ምግባራዊ የስፖርት እሴቶች አወንታዊ ለውጥ ለማምጣት ያለው አቅም ከፍተኛ ነው፡፡ ነገር ግን አውንታዊ ተጽኖው በብልሹ አሰራሮች ምክንያት ሲጓደል ትልቅ ጉዳት ያመጣል፤

በአጠቃለይ በዘርፉ ውስጥ ያለው ሙስና ሁሉንም የሚኒስቴሩን ዘርፎች ብሎም የፌዴሬሽኖችን፣ የክለቦችን እና የአትሌቶችን የፋይናንስ አሰራር ይጎዳል ፡፡ በተጨማሪም በሚታዩ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ምክንያት ዘርፉ የህዝባዊ አመኔታን ማጣት በባህላዊ እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅእኖ ያደርሳል (Nowak & Nowak, 2021) ፡፡ ከዘርፉ የሚጠበቀዉንም ሀገራዊ አስጠዋጽኦ እንዲዳከም ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡




### 3.1.1. በተቋሙ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳቶች

የተናጠል ስራ እንዲበራከትና ቅንጅታዊ አሰራር እንዳይኖር ያደርጋል፤ስራዎችን በመናበብ እንዳይሰሩና ተመሳሳይ ተግባራት በድግግሞሽ እንዲከናወኑ ያደርጋል፤ያልተገባ የሰው ሃይል፤ የጊዜ፤የገንዘብና የቁሳቁስ ብክነትን ያስከትላል፤ግልጽኝነት፣ተጠያቂነት አንዳይኖር ያደርጋል፣የስራ ግንኙነት መርህ እንዲጣስ ያደርጋል፤ተግባራት በተሟላ ሁኔታ እንዳይከናወኑ ወይም ስራዎች እንዲንጠባጠቡ ያደርጋል፤ስለተቋማቱ የተሟላ መረጃ እንዳይኖር ደርጋል፤ ህብረተሰቡ ስለተቋማቱ የተዛባ መረጃ እንዲኖረው ያደርጋል፤በአጠቃላይ ስርዓት የመጣስና ያልተገባ የሀብት ብክነት ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳቶችና ሌሎችም የብልሹ አሰራሮች ዉጤጦች ተደምረው የሙስና ወንጀል ድርጊቶች እንዲፈጸሙ በማድረግ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዳይወጣ ያደርጋሉ፡፡

**<u>ምሳሌ</u>፡ የፌደራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝት ሪፖርት** 2016

*በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ 9911796.88 ብር እንዲሆም 1200300.00 ለመወራረዱ ማስረጃ አልቀረበም ቀሪ ተሰብሳሚ ድምር የአንድ ርእስ ብቻ 3766793.37 ብር መኖሩን ሳያል፡፡*

### 3.1.2 በሀገር ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች

**ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች**፡-ሙስና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በመፍጠር የአገር ልማት እንዲቀጭጭ፣ የኢኮኖሚ እድገት እንዲገታ፣ ኪሣራና ውድቀት እንዲፈጠርና ድህነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ በማድረግ ዜጎች በከፋ ኑሮ ውስጥ እንዲወድቁ ያደርጋል፡፡ **ማህበራዊ ጉዳቶች**፡-ሙስና በዜጎች ላይ የኖራል ውድቀት ፣ የሥነምግባር ቀውስ እና የሕግ የበላይነት እንዳይሰፍን በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ /ሥራ አጥነት፣ ጎዳና ተዳዳሪነት፣ ሥርዓተ አልበኝነት፣ ወዘተ ያስከትላል፡፡ **ፖላቲካዊ ጉዳቶች**፡- ሙስና ህዝብ በመንግስትና በሕግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣና በዲሞክራሲ ሥርዓት ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው በማድረግ ፖለቲካዊ አለመረጋጋ ት እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡ **አከባቢያዊ ጉዳቶች**፡-ሙስና የስግብግብነት ስሜትን አግንኖ ስለሚያወጣ የተፈጥሮ ሚዚንን በማዛባት ከባቢያዊ ሁኔታዎችን የሚያዛቡ ተግባሮችን በመፈጸም የሰውን ሌጅ የመኖር ህሌውና የሚፈታተኑ ጉዳቶችን ያስከትላል፡፡

## 3.2 በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶች

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

ችግሩ ከተከሰተ በኂላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ ንኡስ ርእስ ስር በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ቀርበዋል፡

### 3.2.1 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቅው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

### 3.2.2 ወቅታዊ የተጋላጭነት ጥናት ዳሳሳ ማድረግ

ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት ከሙስናና ብልሹ አሠራሮች የፀዳ የማድረግ ሥራ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ በየጊዜው፣ በየዘመኑ፣ በየወቅቱ እየተቀያየረ የሚመጣውን የሙስና ባሕሪ በመለየት ተመጣጣኝ ብቻ ሳይሆን ቀዳሚ (proactive) የሆኑ ሥልቶችን በመቀየስ የማምከን ሥራ ለመስራት ሁል ጊዜ የአሰራር ግድፈቶችንና ሙስናን በጥናት ለይቶ ማጋለጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

በኮሚሽኑ (በ2015 ዓ.ም) የሙስና ስጋት ግምገማ ጥናት መሰረት በባህልና ስፖርት ዘርፍ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አምስቱ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራርን በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ስለማካሄዳቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም የሚያሳየው በዘርፉ ያሉ ተቋማትን ለሙስና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት ግልጽነትና ተጠያቂነት ከመፍጠር አኳያ የተጠናከረ ስራ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ነው፡፡ በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የደንበኛ እርካታ በገለልተኛ አካል ስለማስጠናታቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ ይሁን እንጂ ብሄራዊ ቤተመዛግብት

የደንበኞች እርካታ በተቋሙ የለውጥ አመራር ዳይሬክቶሬት ያስጠና መሆኑን ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በባህል እና ስፖርት ዘርፍ ስር በሚገኙ አንዳንድ ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት አለማድረጋቸው፣ የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል አለማስጠናት፣ በተወሰኑ ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) አለመኖር እና ጥቆማን መሰረት አድርጎ የቅድመ መከላከል ስራ ያለመስራት ችግር በደንበኞች ሊነሱ የሚችሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት አስቸጋሪ ከማድረጉም በላይ የተጠያቂነት ስርአት ለመዘርጋት አዳጋች ይሆናል፡፡

የሙስና ስጋት ጥናት ስራን በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በተቋሙ ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችንና የስጋት ዓይነቶችን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ የሙስና ስጋት መለያ ጥናት ሂደት የሚጠይቅ ሲሆን የጥናቱን መሠረታዊ ዓላማዎች መለየት፣ መጠይቅ ማዘጋጀት፣መረጃ መሰብሰብ፣ መንስኤዎችን መለየትና የዉጤት ሪፖርት ማቅረብ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተቋም ውስጥ የሙስና ስጋት አካባቢዎችን ለመለየት የተለያዩ ስልቶችን እና የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ይቻላል፡፡ በተለይም ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሠራር በምንና እንዴት በተቋሙ ውስጥ ሊከሰት እንደሚችል የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ መረጃዎች በግብዓትነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

- ከተቋሙ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን መሰብሰብ፤
- የሥጋት ቦታዎችን፤ ሂደቶችን / ተግባራትን መለየት፤
- የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የዜጎች ቅሬታዎች፣ የጠቋሚዎች መረጃ ፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ እና ከዚህ በፊት ያጋጠሙ የሙስና ጉዳዮች፣
- የሁኔታዎች ትንተና (የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች፣ የህዝብ አስተያየቶች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ የሥራ አካባቢ ውስጣዊ ቅኝቶች፣ ከሠራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለመጠይቆች)

- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች (ግልጽ ያልሆኑ የህግ ማዕቀፎች፣ የውስጥ ደንቦች እና ሂደቶች፣ ያልተጣጣሙ (inconsistent) የመተዳደሪያ ደንቦች፣ ለተመሳሳይ ጉዳይ የወጡ የተለያዩ ደንቦች፣ ወዘተ)፣
- ሁሉንም የሙስና ስጋቶች በአንድ ጊዜ ለመቅረፍ አዳጋች በመሆኑ ዋነኛ ናቸው ተብለው የሚገመቱትን በደረጃ መለየት ያስፈልጋል፡፡

### 3.2.3 ግልጽነትን ማስፈን

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

### 3.2.4. ተጠያቂነትን ማስፈን

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡ ፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

### 3.2.5 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው። በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውሰጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል። የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል። በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው። የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡ የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው። በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል።

### 3.2.6 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው። የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል። ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል።

### 3.2.7 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡ ፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

### 3.2.8. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና የዋና ስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

### 3.2.9 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቻ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣

- የጥቅም ግጭትን የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

### 3.2.10 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡ እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል፡፡

### 3.2.11 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡



(ምንጭ ፡ ከኮሚሽኑ የቴሌግራም ገጽ)




(ምንጭ ፡ የኮሚሽኑ የቴሌግራም ገጽ)

## ➢ የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በአለም አቀፍ፣ አፍሪካ እና ኢትዮጵ ደረጃ የስነ-ምግባር ጉድለቶች፣ብልሹ አሰራሮችና የሙስና ወንጀሎች ልማትን በማዳከም የሀገር ኢኮኖሚ እንዲገታ፣ የሞራልና የሥነምግባር ቀውስ እንዲባባስ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር፣ ህዝብ በመንግስትና በህግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርጉ አለማቀፋዊና ብሔራዊ ተግዳሮቶች

ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

## ➢ የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከሰራችሁ በኋላ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

| | ዘርፍ / የስራ ሂደት | የደረሰዉ / የሚያደርሰው ጉዳት |
|---|---|---|
| | በብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ | |
| | በኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር | |
| | በብሔራዊ ቤተመዛግብት እና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት | |
| | በየኢትዮጵያ ስፖረት አካዳሚ | |
| | በዋናው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት | |
| | በግዢ ሂደት | |
| | በጫረታ ሂደት | |
| | በፋይናነስ ሂደት | |
| | በግንባታና እድሳት ፕሮጀክቶቸ አስተዳደር ሂደት | |
| | በፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ሂደት | |
| | በስልጠና ዘርፍ ሂደት | |
| | በኦዲትና ቁጥጥር ሂደት | |
| | ሌሎች | |

2. በዘርፉ ባሉ የስራ ሂደቶች ውስጥ የተከሰቱት የሙስና ወንጀሎች በተቋም ላይ ብቻ ጉዳት ያመጡ ናቸው ወይስ ሀገራዊ ጉዳትም ኣላቸው፡፡ ጉዳታቸው የኢኮኖሚ ብቻ ነው ወይስ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳት ያስከተሉ ስለመሆናቸው የቀደመ ምልከታችሁን መሰረት በማድረግ በብድን ተወያይታችሁ ሀሳባችሁን ለተሳታፊዎች አቅርቡ ፡፡

4. በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ስር የሚገኙና በሰንጠረዡ ዉስጥ የተዘረዘሩት ዘርፎች ወይም የስራ ሂደቶች ውስጥ የተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ በብልሹ አሰራሮች እና ሙስና ወንጀሎች ምን ጉዳት ሊያደርሱ እንደሚችሉ በቡድን ገምግማችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡
5. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶችን ዘርዝሩ፡፡
6. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡
7. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡

## የመረጃ / ማጣቀሻ/ ምንጮች


Abiy, W. (2018). The Hefty Footballers' salary. Ethiopian Business Review, 8(81).

Abiy, W. (2020). Football federation facing financial Distress. Ethiopian Business Review, 8.

Africanews.com (2022). Ethiopian distance runner and Olympic Finalist banned 5

years for Doping.

Dalena, A. (2016). *Protecting Cultural Heritage in Times of Instability Tunisia, a case study.* (Faculty of Juridical, Political and Social Sciences of Tunis Master's Degree in Democratic Governance), University of Carthage,

Fabrice, C. (2016). Sweden's Abeba Aregawi won the world outdoor 1500m title in 2013. The Guardian

Hwang, G. (2016). Understanding Sport Corruption: An Examination of People's Perceptions Toward Corruptions. *Journal of Psychology Research, 6*(4). doi:10.17265/2159-5542/2016.04.005

Masters, A. (2015). Corruption in sport: From the playing field to the field of policy. *Policy and Society, 34*(2), 111-123. doi:10.1016/j.polsoc.2015.04.002

Nassif, N. (2014). Corruption in Sport. *Middle East Law and Governance, 6*(2), 123-140. doi:10.1163/18763375-00602003

Nowak, L., & Nowak, M. A. (2021). Impact of European Union programs on the activities of the Third Polish Republic's Parliament in the field of sport in the years 2004-2007. *Central European Journal of Sport Sciences and Medicine, 33*, 17-25. doi:10.18276/cej.2021.1-02

Ole, S. (2016 ). *Corruption in football: mechanisms, actors and drivers.* (This master's thesis is carried out as a part of the education at the University of Agder and is therefore approved as a part of this education. However, this does not imply that the University answers for the methods that are used or the conclusions that are drawn.), University of Agder,

Peter, V., Alice, S., Peter, W., & Rory, D. (2017). *Global Anti-Bribery Guidance: Best Practice For Companies in the UK and overseas* Transparency International UK

Samson, W., Hirko, T., & Asim, K. (2017). Biomechanics of Javelin throwers in the case of selected Oromia athletics clubs. International Journal of Physical and Social Science. 7(6).pp130-146

Siegel, D. (2016 ). Lights, Cameras, and FCPA Actions: The Problem of Foreign Corrupt Practices by Hollywood *Entertainment, Arts and Sports Law Journal, 27* (3).

The Reporter Megazine (2019). Ethiopian athlete tests positive for doping.

UNODC. (2019 ). United Nations Office on Drugs and Crime: Regional Programme for South Eastern Europe, 2020-2023. 2-172.

UNODC. (2021). *Global Report on Corruption in Sport Evolutions in sport related to corruption*.

ኢንፍራስትራክቸር ትራንስፓራንሲ ኢንሼቲቭ ኢትዮጵያ (2016) የአደይ አበባ ስታዲየም ግንባታ ፕሮጀክት ጥናት ሪፖርት

የፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2016)፤ሙስናን መታገል በተግባር (የማሰልጠኛ ሞጁል)

ፌዴራል ዋና ኦዲተር (2016) የባህል እና ስፖርት ሚኒሰቴር የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ፣ አዲስ አበባ።

ዓለማየሁ, ግ. (ነሐሴ 16 ቀን 2016 ዓ.ም). አትሌቲክሱ ችግር ውስጥ የገባው በአደረጃጀትና አመራር ክፍተት ነው. *አዲስ ዘመን ሐሙስ*

ኮሚሽን, የ. የ. እ. የ.-ሙ. (2015). *የባህልና ስፖርት ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት*. አዲስ አበባ

## አባሪ አንድ ፡ የቅድመ ስልጠና ዳሳሳ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ ስልጠናው ከመጀመሩ በፊት በሰልጣኞች የሚሞላ ሲሆን፤ ዓላማውም ሰልጣኞች ከስልጠናው ብፊት ስለ ስልጠናው ይዘቶች ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት እንዲሁም ከስልጠናው መጨረሻ ላይ እንዲያገኙ የሚጠበቀውን እውቀት ፤ ክህሎት እና የአመለካከት ለውጥ እእንዲያገኙ ለማስቻል በስልጠናው ወቅት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አሳልጣኞች መለየት እንዲችሉ መድረግ ነው። ስለዚህ የስልጠናዉ ዓላማ እንዲሳካ ሰልጣኞች መጠይቁን በመሙላትና ትክክለኛውን መልስ በመስጠት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

| | |
|---|---|
| | **ክፍል 1. የሰልጣኞች አጠቃላይ መረጃ (በተሰጠው ቦታ ላይ መልሱን ይጻፉ)** |
| 1.1 | ፆታ ፡ |
| 1.1 | የመጡበት መስሪያ ቤት ፡ |
| 1.2 | የትምህርት ደረጃ ፡ |
| 1.3 | የሚሰሩበት መደብ ፡ |
| | **ክፍል 2. ሰልጣኞች ያላቸው የቀደመ ግንዛቤ እና አመለካከት (በሚመርጡት መልስ ላይ በማከበብ ያመልከቱ)** |
| 2.1 | ከዚህ በፊት በሥነምግባር /በሰራ ሥነምግባር ላይ ስልጠና ወስድዋል? ወስጃለሁ / አልወስደኩም |
| 2.2 | ከዚህ በፊት በሙስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮች ላይ ስልጠና ወስድዋል? ወስጃለሁ / አልወስደኩም |
| 2.3 | የሰራተኞች ሥነምገባር ጉድለት ከብልሹ አሰራር መኖር ጋር ተያያዥነት አለው? አለው / የለውም |
| 2.4 | የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሰራተኞች የሙስና ወንጀልን ለመከላከል ስለ ሙስና ወንጀል ምንነት በቂ ግንዛቤ ነበራቸው ብለው ያምናሉ? ኣዎን አምናለሁ / ኣይ አላምንም |
| 2.5 | የሙስና ወንጀል ገንዘብ በመቀብል የሚፈጸምን ጉቦ ብቻ ይመለከታል። ትክክል ነው / ትክክል አይደለም |
| 2.6 | በአሁኑ ወቅት የሙስና ወንጀል በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ችግር ነው። ትክክል ነው / ትክክል አይደለም |
| 2.7 | በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ዘርፎች ውስጥ የሙስነ ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮች አሉ። አዎን ኣሉ / ኣይ የሉም |
| 2.8 | በምሰራበት መስሪያ ቤት የሰራተኞች የሥነምግባር ጉድለት አይታይም። ትክክል ነው / ትክክል አይደለም |
| 2.9 | በምሰራበት መስሪያ ቤት ብልሹ አሰራሮች አይስተዋሉም። ትክክል ነው / ትክክል አይደለም |
| 2.10 | በምሰራበት መስሪያ ቤት የሙስና ወንጀሎች ተስተውለው ያቃሉ። ኣዎን ያቃሉ / ኣይ ኣያቁም |
| 211 | በምሰራበት መስሪያ ቤት የሙስና ተጋላጭነትን በመለየት ረገድ ተሳትፎ ነበረኝ። ኣዎን ነበረኝ / አይ አልነበረኝም |
| 2.11 | የባህል እና ስፖርት ዘርፍ ሰራተኞች የሙስና ወንጀልን ለመከላከል በቂ ክህሎት ነበራቸው ብዬ ኣምናለሁ። አዎን አምናለሁ / ኣይ ኣላምንም |
| 2.12 | በባህል አና ስፖርት ዘርፍ ከዚህ በፊት የሙስና ወንጀሎችን እና ብለልሹ እሰራሮችን ስመለከት ጥቆማ እቅርቤ አቃልሁ። አዎን ኣቃለሁ / አይ አላዉቅም |
| 2.13 | የሙስና ወንጀሎችን አና ብለልሹ እሰራሮችን ብመለከትም በኂላ ችግር ይደርስብኛል ብዬ ስለምፈራ ጥቆማ አላቀርብም። ኣዎን አላቀርብም / ኣይ ኣቀርባለሁ |
| 2.14 | ብለሹ አሰራሮችን እና የሙስና ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያሰችሉ ስልቶችን ለይቼ መዘርዘር አችላለሁ። ኣዎን አችላለሁ / አይ አልችልም |
| 2.15 | በባህል እና ስፖርት ዘርፍ ብልሹ አሰራሮች እንዲሁም የሙስና ወንጀሎች ቢኖሩም ሀገራዊ ጉዳት የሚኖራቸው አይደሉም። ትክክል ነው / ትክክል አይደለም |
| | **ክፍል 3 ፡ ሰራተኞች ክሰልጠናው የሚጠብቁት ውጤት** |
| | **ከዚህ ስልጠና ምን አገኛልሁ ብለው እንደሚጠብቁ በአጭሩ ይጥቀሱ።**<br>1. ____________________<br>2.____________________<br>3.____________________<br>4.____________________<br>5.____________________ |

## አባሪ ሁለት፡ የራስ መገምገሚያ ቼክሊስት

ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አምስት ስር የቀረቡትን ይዘቶች በተመለከተ በምን ያህል እንደተረዳችሁ እና ይዘቶቹ ለእውቀት፣ክህሎትና ለአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ምን ያህል እንደጠቀሟችሁ የግል ግምገማችሁን ከ1 - 5 በተሰጡት መስፈርቶች መሰረት ከይዘቱ ፊት ለፊት የተሰጡትን ቁጥሮች በማክበብ አመልክቱ፡፡

1 = በፍጹም አልስማማም   3 = በመጠኑ እስማማለሁ   5 = በጣም እስማማለሁ
2 = አልስማማም   4 = እስማማለሁ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **1. የሙስና ወንጀል ይዘቶችን በተመለከተ** | | | | | | |
| 1.1 | የሙስና ወንጀል ምንነት ተረድቻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1.2 | የሙስና ወንጀል አይነቶችን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1.3 | የሙስና ወንጀል የሚያስክትላቸዉን ችግሮች መግለጽ እችላለው፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| **2. የባህል እና እስፖርት ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ያለውን ተጋላጭነት በተመለከተ** | | | | | | |
| 2.1 | ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ለይቻለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2.2 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትርን የሙስና እና የብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ሁኔታ ለይቻለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2.3 | ብሔራዊ ቤተ-መዛግብትን የብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ሁኔታ ለይቻለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2.4 | የኢትዮጵያ ስፖረት አካዳሚን የብልሹ አሰራር ተጋላጭነትን ሁኔታ ለይቻለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2.5 | በብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲን የሙስና እና የብልሹ አሰራር ተጋላጭነትን ሁኔታ ለይቻለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2.6 | ዋናው የሚኒስቴር መስሪያ ቤትን የሙስና እና የብልሹ አሰራር ተጋላጭነትን ሁኔታ ለይቻለሁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| **3. በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በተመለከተ** | | | | | | |
| 3.1 | በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን አለያለሁ ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.2 | በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚከሰቱባቸውን ምክንያቶች እዘረዝራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.3 | የተቋማት አደረጃጀት ክፍተት እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን አሰርዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.4 | የተጠያቂነት አለመስፈን እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.5 | በተቋሙ ግልጽነት አለመኖር እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን አብራራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.6 | አዋጆችን፣ደንቦችንና መመሪያዎችን አለመተግበር እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.7 | የንብረት አስተዳደር ጉድለትን እንዴት በተቋሙ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.8 | የግዢ ስርዓት ችግር እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.9 | የሰው ሀብት አስተዳደር ክፍተት እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.10 | የኦዲትና ቁጥጥር ግኝት አለማስተካከል እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን ማብራራት እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3.11 | የፕሮጀክቶች አስተዳደር ጉድለት እንዴት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ምክንያት እንደሚሆን ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| **4. በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች በተመለከተ** | | | | | | |
| 4.1 | በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች በተቋም ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳቶች እለያለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.2 | በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች በሀገር ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳቶች እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 4.3 | በባህል እና ስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች በተቋሙ ስር በሚገኙ መስሪያ ቤቶች እና የስራ ሂደቶች ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳቶች ለይቻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| **5. በዘርፉ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶችን በተመለከተ** | | | | | | |
| 5.1 | የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልቶችን አስፈላጊነት እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.2. | የሙስና እና የብልሹ አሰራሮችን መከላከያ ስልቶች እዘረዝራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.3. | የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶችን መተግበር እችላለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.4 | ግልጽነጽን ማስፈን እንዴት ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንደሚስችል አብራራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.5 | ተጠያቂነትን ማስፈን እንዴት ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንደሚስችል እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.6 | ቴክኖሎጂን ትቅም ላይ ማዋል እንዴት ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንደሚስችል አብራራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.7 | የሰራተኞችንአቅም ማጎልበት እንዴት ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንደሚስችል አስረዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.8 | የስነምግባር ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ እንዴት ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንደሚጠቅም አብራራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.9 | ሀብትን ማሳወቀና ማስመዝገብ እንዴት ሙስናን ለመከላከል እንደሚረዳ እገልጻለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.10 | የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን ማስቀረት እንዴት ሙስናን ለመከላከል እንደሚረዳ አብራራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.11 | የዘርፉን የሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ሚና የስራ አካል አድርጎ መተግበር እንዴት ሙስናን ለመከላከል እንደሚረዳ እተነትናለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.12 | የመንግስት የስራ ሀላፊዎች ሙስናን የመታገል ሚናን ማጠናከር እንዴት ሙስናን በመከላከል ረገድ አስተዋጽዖ እንዳለው አብራራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5.13 | ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት መስራት እንዴት ሙስናን ለመከላከል እንደሚያስችል አስረዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| **6. አጠቃላይ የይዘት አቀራረቡን በተመለከተ** | | | | | | |
| 6.1 | የግል ሰራዎች እና የቡደን ውይይቱ የቀረበውን ይዘት ለመረዳት ረድተውኛል | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6.2 | የቀረቡት መሳሌዎቸ የምዕራፍ ሁለትን ይዘቶች ለመረዳት ረድተውኛል | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6.3 | የቀረቡት ማሳያ ስእሎቸና ዲያግራሞች ይዘቶችን ለመረዳተ አጋዥ ነበሩ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

# አባሪ ሶስት፡ ለሰልጣኞች የተዘጋጀ ተጋላጭነት ልየታ መለማመጃ

በሚከተለው ሰንተረዥ ውስጥ የቀረቡት የዘርፉ የስራ ሂደት ትኩረቶች ሲሆኑ የበለጠ ለሥነ-ምግባር ጉድላት፣ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና የተጋለጠ መሆኑን ከቀረቡት 0-5 ደረጃ ቁጥሮች ውስጥ የእናንተን የቀደመ መረጃ መሰረት በማድረግ የሚያገኘውን ውጤት አክብቡበት፡፡ ቀጥሎም በየዘርፉ የተገኘውን ድምር ውጤት ለየዘርፉ እንዲሁም ለሥነምግባር ጉድለት፤ ለብልሹ አሰራርና ለሙስና ወንጀል የሁሉም ዘርፍ ድምር እና አማካይ ውጤት አስቀምጡ፡፡ በመጨረሻም የቡድኖች አጠቃላይ ውጤት ተደምሮ ለተሳታፊዎች ይቀርባል፡፡

0 = ምንም የለም    2 = በመካከለኛ ደረጃ አለ    4 = በጣም በከፍተኛ ደረጃ አለ

1= በመጠኑ አለ    3 = በከፍተኛ ደረጃ አለ    5 = ምንም መረጃ የለኝም

| | የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዋና ዋና የስራ ዘርፎች | የተጋላጭነት ደረጃ መስፈሪያ ነጥቦች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር** | | | | | | |
| 1 | የስራ ሥነምግባር ጉድለት | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | ብልሹ አሰራራሮች | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3 | የሙስና ተግባር / ወንጀል | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **ብሔራዊ ቤተ-መዛግብት** | | | | | | |
| 1 | የስራ ስነምግባር | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | ብልሹ አሰራሮች | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3 | የሙስና ተግባር/ ወንጀል | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **የኢትዮጵያ ስፖረት አካዳሚ** | | | | | | |
| 1 | የስራ ስነምግባር ጉድለት | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | ብልሹ አሰራራሮች | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3 | የሙስና ተግባር /ወንጀል | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **በብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ** | | | | | | |
| 1 | የስራ ስነምግባር ጉድለት | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | ብልሽ አሰራራሮች | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3 | የሙስና ተግባር /ወንጀል | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **ዋናው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት** | | | | | | |
| 1 | የስራ ስነምግባር ጉድለት | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2 | ብልሹ አሰራራሮች | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3 | የሙስና ተግባር /ወንጀል | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |